# 1.3 ይዛትን በሳ.ሜ$^3$ በሜ$^3$ እና በሊትር መለካት

ከዚህ በታች ለተቀመጡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን ምላሽ ምረጡ

1. አቶ ሄኖክ የ 5 ሊትር የሚይዝ ጀሪካን አለው ። ጀሪካኑን ለመሙላት ስንት የ 500 ሚ.ሊ. የሚይዙ የሃይላንድ እቃዎች ያስፈልጋል ?

   ሀ) 8 ለ) 10 ሐ) 5 መ) 20

2. በአንድ ካፍቴሪያ ውስጥ ካለው 3 ሊትር ጁስ 1200 ሚ.ሊ. ሊትር የሚሆነው ለተጠቃሚዎች ቢሸጥ ካፍቴሪያው ስንት ሚ.ሊ. ጁስ ይቀረዋል ?

   ሀ) 1.8 ለ) 2.5 ሐ) 1.5 መ) 2

3. አንድ የነዳጅ ማደያ ድርጅት 10ሜ$^3$ እቃ ውስጥ የተቀመጠ የነዳጅ ዘይትን ለመኪናዎች ሲያከፋፍል ለአንድ መኪና 300 ሊትር ቢሰጥ በጠቅላላው ለስንት መኪናዎች ማከፋፈል ይችላል ?

   ሀ) 25 ለ) 40 ሐ) 30 መ) 15

LIVEWORKSHEETS

3.1. የነዳጅ ማደያው ምን ያህል ሊትር ነዳጅ ይተርፈዋል ?

ሀ) 11 ለ) 20

ሐ) 15 መ) ምንም አይተርፈውም

4. 6ሜ$^3$ ውሃ ወደ 6000 ሳ.ሜ$^3$ ውሀ ወደሚይዝ እቃ ለመገልበጥ ቢያስፈልግ ምን ያህል እቃዎች ያስፈልጉናል ?

ሀ) 200 ለ) 1000 ሐ) 300 መ) 1500

5. አንድ ወርዱ10 ሜ፣ ርዝመቱ 18 ሜ እና ጥልቀቱ ደግሞ እና 8 ሜ ስፋት ያለው ገንዳ ለመሙላት ምን ያህል ውሃ ያስፈልጋል ?

ሀ) 400 ኪ.ሊ. ለ) 400,000 ሊ

ሐ) 40,000 ሊ. መ) ሀ እና ለ

6. 2000 ሊትር ውሃን ርዝመቱ 15 ሜ እና ወርዱ 10 ሜ የሆነ የዋና ገንዳ ውስጥ ገልብጦ ለመጨረስ የገንዳው ጥልቀት ስንት መሆን አለበት?

ሀ) 15 ለ) 20 ሐ) 8 መ) 12

7. 10 ሊትር ውሃን ከ ባልዲ ውስጥ 600 ሚሊ ሊትር የሚይዙ የሃይላንድ እቃዎች ውስጥ ለመገልበጥ ምን ያህል የሃይላንድ እቃዎች ያስፈልጋሉ ?

ሀ) 18 ለ) 22 ሐ) 16 መ) 20

7.1. ምን ያህል ሚሊ ሊትር ውሃ ይተርፋል ?

ሀ) 200 ለ) 20

ሐ) 400 መ) ምንም አይተርፍም

8. አንድ የስፖርት ክለብ ርዝመቱ 40 ሳ.ሜ ወርዱ 40 ሳ.ሜ እና ጥልቀቱ 40 ሳ.ሜ የሆኑ ሎከሮች አሉት ፡፡ ሎከሮቹ የሚይዙት መጠን በ ሜ$^3$ ምን ያህል ይሆናል ?

ሀ) 64 ሜ$^3$ ለ) 6.4 ሜ$^3$

ሐ) 0.64 ሜ$^3$ መ) 0,064 ሜ$^3$

LIVEWORKSHEETS

9. እናቴ እቤት ውስጥ ለምታዘጋጃቸው 50 ኩኪሶች ግማሽ ሊትር ወተት ያስፈልጋታል ፡፡ አንድ ኩኪስ ምን ያህል ሚ.ሊ. ወተት ያስፈልጋታል ?

ሀ) 10 ሚ.ሊ.  ለ) 2 ሚ.ሊ.  ሐ) 4 ሚ.ሊ.  መ) 1 ሚ.ሊ.

10. 5000 ሊትር የሚይዝ የውሃ ታንከር ርዝመቱ 1ሜ፣ ወርዱ 3ሜ እና ጥልቀቱ ደግሞ 3ሜ የሆነ ገንዳ መሙላት ይችላል ወይስ አይችልም ?

ሀ) ይችላል  ለ) አይችልም

10.1. ምን ያህል ሜርት ኪዩብ ውሀ ተጨማሪ ያስፈልጋል ?

ሀ) 2 ሜ$^3$  ለ) 4 ሜ$^3$  ሐ) 5 ሜ$^3$  መ) 3 ሜ$^3$

<u>ከዚህ በታች ለተቀመጡት ዝርዝሮች ተስማሚ የሆነውን የመለኪያ መጠን ምረጡ</u>

1. የብርጭቆ ውሀ .....................
2. የኩባያ ሻይ .....................
3. የመኪና ነዳጅ.....................
4. የጥርስ ኮልጌት .....................
5. የመዋኛ ገንዳ ውሀ .....................
6. የፀሀይ መከላከያ ቆዳ ክሬም .........................

LIVEWORKSHEETS